# የፌደራል ማግሥት ገንዘብ ክፍያ
# <u>መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 265/2013</u>

የፌደራል ማግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 203/2013ን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌደራላዊ የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የፌደራል ማግሥት ገንዘብ ክፍያ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 265/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ማሻሻያ</u>

የፌደራል ማግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1/ የመመሪያው አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቷል፡፡

"3 "የክፍያ ዘዴ" ማለት የመንግሥት ገንዘብ ለሚከፈለው አካል ወይም ተቀባይ መሥሪያ ቤት በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወይም በሌትር አፍ ክሬዲት ወይም በገንዘብ ማዛዋወሪያ የማዘዣ ትዕዛዝ ወይም የኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ በማጠቀም የሚፈፀም ክፍያ ነው፡፡"

2/ የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (5) ተሰርዘው እንደቅደም ተከተላቸው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (5) ተተክተዋል፤

"3/ የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ የሚፈፀመው ወይም ወጪ የሚደረገው በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ፣ በሌተር አፍ ክሬዲት፣ በባንክ ዝውውር የክፍያ ማዘዣ በመሙላት ወይም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሣብ በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ በማስተላለፍ ነው፡፡

5/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጀት ዓመቱ ወስጥ የሚከፈሉ የክፍያ ማጠናቸው ከብር 100,000 በላይ የሆኑ ወጪዎች መከፈል ያለባቸው በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በማጠቀም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሣብ በማስተላለፍ ይሆናል፡፡"

3/ የመመሪያው አንቀጽ 8 ንዑስ ንቀጽ (1)(ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) ተተክቷል፡፡

"1(ለ)/ እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያቤት ከተፈቀደለት የገንዘብ ጣሪያ ሳያልፍ ከተከፈተለት የገንዘብ ማስተላለፊያ የባንክ ሂሣብ በቼክ ወይም በገንዘብ ማዛዋወሪያ

ትዕዛዝ ወይም በሌተር ኦፍ ክሬዲት ወይም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ክፍያ ይፈጽማል፡፡"

4/ የመመሪያው አንቀጽ 11 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 11 ተተክቷል፤

"11/ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ በመሥሪያ ቤቱ ገንዘብ ከፋይ በኩል በጥሬ ገንዘብ ወይም ከባንክ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት በቀጥታ በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ወደ ሠራተኛው የባንክ ሂሣብ ቁጥር በማስተላለፍ ሊከፈል ይችላል፡፡"

5/ የመመሪያው አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (3) (መ) እና ንዑስ አንቀጽ (3)(ሸ) ተሠርዘው እንደቅደም ተከተላቸው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3)(መ) እና ንዑስ አንቀጽ (3)(ሸ) ተተክተዋል፡፡

"3(መ)/ ለወሩ ጥቅል የተጣራ የመሥሪያቤቱን የሠራተኛ ደመወዝ የሠራተኛው ስም፣ የባንክ ሂሣብ ቁጥርና የወሩ የተጣራ የደመወዝ መጠን የያዘ ዝርዝር በሁለት ኮፒ በማዘጋጀት ክፍያ ወደሚፈጸመው ባንክ ያስተላልፋል፤

3(ሸ)/ ባንኩ በተላለፈለት ዝርዝር መሠረት የሠራተኛን የተጣራ ደመወዝ ወደ ሠራተኛው የቁጠባ ሂሣብ ካስተላለፈ በኋላ የሠራተኛው ደመወዝ በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ስለመተላለፉ ከባንኩ ሲስተም የሚገኝ ሚረጋገጫ እንደወጪ ክፍያ ማስረጃ ሊቆጠር ይችላል፡፡"

## 3. <u>መመሪያ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ ከ________ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ______ቀን 2011 ዓ.ም**

**አህመድ ሽዴ**
**የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር**